# ሰለዮችን በማጋለጥ ስም የሚደረግ የቂምበቀል ዘመቻ

በዚህ እርዕስ ይህን አጭር ማስታወሻ ለመጻፍ ያስገደደኝ በቅርቡ በተለያዩ በተለይም በኢትዮ ሚዲያ ፎረም በሚባለው ድህረገጽ ላይ በአዘጋጁ በአቶ ክንፈ አሰፋ አቀነባባሪነት በእኔ ላይ ያቀረበውን የሃሰት ክስና ውንጀላ ሙከራ አንብበውና ሰምተው ተመሳሳይ የተሳሳተ አቋም፣ካለምንም መረጃ እንደ ገደል ማሚቶ ተቀብለው የሚያስተጋቡትንና ወደዚያ የተሳሳተ አቅጣጫ ለመግባት አሰፍስፈው የሚጠብቁትን የዋሆች ከስህተት እንዲቆጠቡና እንዲታረሙ ብሎም የትግሉ ሂደት አቅጣጫውን እንዳይስት በዋናው ዙሪያ  እንዲያተኩር ለማሳሰብ ነው።

እርግጥ የተሰነዘረው የስም ማጥፋት ዘመቻ አስጨንቆኝና ዋጋ ሰጥቸው አይደለም።በዚህ ሰዓት አሉቧልታ ከመለዋወጥ የበለጠ ቁም ነገር መሥራት እንዳለበት አምናለሁ።ሆኖም ግን ተንኮለኞች በሚሰሩት የቅሌት ተግባር የሚቃወሟቸውን እውነተኞች በበቀል በመነሳት የሰውን ህልውና በሚነካ መልኩ ዘመቻ የሚያካሂዱና የግለሰቦችን ቀና ተሳትፎና ዓላማ ጥቁር ቀለም በመቀባት ለመነጠል የሚያደርጉትን ዝም ብሎ ማለፉ በአመላቸውና በድርጊታቸው እንዲቀጥሉበት ማበረታታትና መንከባከብ ይሆናል። ስለሆነም በተነሳው የሃሜታ ዘመቻ ላይ የግሌን አስተይየት ለመስጠት ተገድጃለሁ።

የክንፉ አሰፋ ድህረገጽ(የኢትዮ ሚዲያ ፎረም) በአሰራጨው መልእክቱ ከዛም ከዚህም ከተሰበሰበ የቪዲዮ ቅጅ ጋር አጣምሮ በሌላ ሁኔታና ቦታላይ የተሳተፍኩትን ውይይት ለማስረጃነት አቅርቧል።

እርግጥ ነው በአለፉት ብዙ ዓመታት ወደ ኢትዮጵያ ተመላልሻለሁ።የተመላለስኩት ግን ለንግድና ከወያኔ ጋር ለመሞዳሞድ አይደለም።በከባቢ ልማት ስር፣በወጣቶች የሙያ ስልጠና ፕሮግራሞች አማካኝነት እርዳታ እየሰበሰብኩ በዘዴና በጥበብ ከሕዝቡ ጋር እየተሰበሰብኩ፣ከተቃዋሚ ድርጅት አባላትና ደጋፊዎች ጋር እየተወያየሁ፣ከወጣቱ ጋር እየተመካከርኩና የሚፈልገውን ለማድረግ እየጣርኩ እንዲደራጅም ምክር እየሰጠሁ ሰላማዊ ትግሉን ከውጭ ሳይሆን ወያኔ ከተቀመጠበት አገር በድፍረትና በዘዴ በማካሄድ የምችለውን አድርጌአለሁ።በአጋጣሚም ዱሮ የማውቃቸውን በሥልጣን ላይ የተቀመጡትን ሳልፈራ መንግሥት በሚከተለውና በሚያደርገው ላይ ጥያቄ እያነሳሁ ለሚሰጡት አስተያየት የራሴን እያቀረብኩ ከመከራከር ወደኋላ አላልኩም።ወደምኖርበት አገርም ስመለስ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ተጨባጭ ሁኔታ “ትዝብት”በሚለው አምዴ በተከታታይ እያወጣሁ እውጭ ለሚኖረው ኢትዮጵያዊ በማቅረብ (በብዛት ኢትዮ-ሚዲያ ላይ ወጥቷል)ቢያንስም ቢበዛም አስተዋጽኦ አድርጌአለሁ።በዚሁ በክንፈ አሰፋ ድህረገጽ ተለጥፎ የወጣውን የቪዲዮ ድራማ በሚመለከት ፣ ሁኔታው የተካሄደው የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ ነበር።የተደረገውን ሁሉ በወቅቱ በትዝብትቁጥር 11 ላይ አይውሉ ውዬ በሚለው ስር ገልጨዋለሁ።በኢትዮ ሚዲያም ወጥቶ ለአንባቢ ቀርቧል፤በዚሁ ድህረገጽ የጽሁፍ ካዝና (አርችፍ)ውስጥ ገብቶ መመልከት ይቻላል።ካልተቻለም ኮፒውን ለመላክ ዝግጁ ነኝ። በወቅቱም ከዚሁ ከክንፉ አሰፋ ከሚባለው ጉደኛ ጋር ተወያይተንበት ነበር ግን የወያኔ ሰላይ ሥራ ነው ብሎ ትችት አልሰጠበትም።እስከቅርብ ጊዜም ድረስ እኔን

በቀና ዓይን እየተመለከተ ሰላምታ እንለዋወጥ ነበር።አሁን በዚህ ተራ አሉቧልታ ቂሙን ሊወጣ የቻለበት ምክንያቱ እንደሚከተለው ነው።

በ2010 ዓ.ም.በበጋው ወር ውስጥ በአመስተርዳም ከተማ ውስጥ የአውሮፓ ስፖርት በዓል ተካሂዶ ነበር።ለዚያ በዓል አዘጋጅነት ከተመረጡት ሰዎች መሃል ክንፉ አሰፋ አንዱ ነው።በዓሉ ተጠናቀቀና የሥራ ዘገባው የወጭ ገቢው ጉዳይ ሲነሳ ችግር ተፈጠረ።ብዙ ገንዘብ አለአግባብ መባከኑ ቅራኔ ፈጠረ።በተለይም የዝግጅቱ ተጠባባቂ የነበረው የአመስተርዳሙ የኢትዮጵያውያን ማህበር ቅርንጫፍ ስለነበር ስለዝግጅቱ አካሄድና ውጤት ለመግለጽ ስብሰባ ጠርቶ የተፈጠረውን ችግር በይፋ ገለጸ።በተለይም የገንዘቡ ጉዳይ ብዙ ሃሜታና እንዲሁም በእንግድነት ከውጭ የመጡት ተዘረፍን ብለው አቤቱታና ቅሬታ በማሰማታቸው በገቢና በወጭው ዙሪያ ምርመራና ጥናት እንዲካሄድ አንድ የሂሳብ መርማሪ(ኦዲተር )ቡድን ተቋቁሞ ውጤቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያሳውቅ ተወሰነ።የተመደበው የኦዲተር ቡድን ሥራውን ጀምሮ አስፈላጊውን የገቢና ወጭ ደረሰኞች(ሰነዶች)ቢጠይቅ የበዓል አዘጋጁ ኮሚቴ(ቡድን)ሙሉ ለሙሉ ሳይሆን ያልተሟላና ኦርጅናል ያልሆነ ኮፒ በመስጠት አልተባበርም አለ። የተመረጠው ሂሳብ አጣሪ ኮሚቴ ምንም ሊያደርግ ባለመቻሉና አንዳንዶቹም ከጭቅጭቁ ለመዳን ጥለው በመውጣታቸው የቀሩት ሃላፊነታቸውን ለማውረድ ስብሰባ እንዲጠራ ጠየቁ።ማህበሩም የተፈጠረውን ችግር ስብሰባ በመጥራት ለአባላቱ አሳወቀ።

በስብሰባው ላይ ከተገኙት መካከል አንዱ ነበርኩ።ብዙ ከተወያየን በኋላ እንደገና በነበሩትና ሌሎችም ተጨምረውበት ሌላ የኦዲተር ኮሚቴ ተቋቋመ፤የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴውም የተጠየቀውን ሰነድ ሁሉ እንዲሰጥና ሙሉ ትብብር እንዲያደርግ ተጠየቀ።ለመተባበርም ቃል ገቡ።ተጣርቶ በአንድ ወር ተኩል ጊዜ ውስጥ ለስብሰባ እንዲቀርብ ተወሰነ።ሆኖም ግን አሁንም እንዳለፈው ጊዜ የበዓል አዘጋጁ ቡድን አሻፈረኝ ብሎ የተጠየቀውን ሰነድ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆን ሥራው ከአራት ወር በላይ ወሰደ።በመጨረሻውም ኦዲተር ኮሚቴው በኮፒና በሽርፍራፊ ደረሰኞች የተደገፈ የሂሳብ ሪፖርቱን ከገጠመው ችግር ጋር አያይዞ፣የገባውንና የጠፋውን ሂሳብ ከታየው የአሰራር ጉድለት ጋር የሚያብራራ ሪፖርቱን አቀረበ።አሁንም የበዓል አዘጋጁ ኮሚቴ (ቡድን)በስብሰባ ላይ የበኩሉን ለማስረዳት ሞከረ።ከዋና ተዋናውያኖቹ መካከል ክንፈ አሰፋ በቦታው አልተገኘም ነበር።የቀረበውን የግራና ቀኙ፣ሃሳብ ማለትም የሂሳብ አጣሪውንና የበዓል አዘጋጅ ኮሚቴውን መግለጫ በማገናዘብ ከተሰብሳቢው ልዩ ልዩ አስተያየቶች ተሰነዘሩ።እኔም እንደተሰብሳቢነቴ የግል አስተያየቴን ሰጠሁ።ሰነድና ደረሰኝ በአግባቡ አለማቅረብ ስህተት እንደሆነና በተለይም ለዝግጅቱ ማካሂጃ በነበረው የገንዘብ እጥረት ሳቢያ በአቶ ክንፉና በሌሎቹ በኩል የተገኘው ብድር አላግባብ ወለድ የተጠየቀበትና የተከፈለበት መሆኑን፣ሌላ ሌላውም ተጨማምሮ የበዓል አዘጋጁ ኮሚቴ አደራውን በሚገባ እንዳልተወጣ ገለጽኩ።በተለይም በአለንበት አገር በባንኮች የማይጠየቀው የብድር ወለድ አይን ያወጣ ዘረፋ መሆኑን ለማሳየት ሞከርኩ።ባንኮች እንኳን ላበደሩት ወለድ የሚያስከፍሉት በዓመት ሂሳብ ነበር፣በበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴ አባል በሆነው በክንፈ አሰፋ በኩልና በሌሎችም ለተገኘው የአንድ ወር ዕድሜ ላለው ብድር የተከፈለው ገንዘብ በ15%ወለድ ሂሳብ የአንድ ሙሉ ዓመት ወለድ ነው። ለ20000ኤሮ ብድር በአንድ ወር ውስጥ 3300 ኤሮ ማስከፈል ዘረፋና እራስን ማበልጸግ

መሆኑን ማንም አይክደውም።በዚሁ ከፍተኛ ወለድ በተጠየቀበት ሂሳብ የአንድወር ብድር ይከፈል እንኳን ቢባል 275 ኤሮ እንጂ ከዚያ አይበልጥም።በልዩ ልዩ መንገዶችም በበዓሉ ላይ የተሳተፈው ሕዝብ የከፈለው ገንዘብና በመጨረሻው በባንክ የሂሳብ ቁጥር የገባው ሲተያይ የሚያሳፍር ነው።በዚህ ሁኔታ የነበረውን አግባብ የሌለው አሠራር  በመቃወሜና እንዲስተካከልም በመጠየቄ የበዓሉ አዘጋጆች የቃላት ዘለፋና ብላክሜል ከመሰንዘራቸውም በላይ አሁን ባልሆነና በማልጠረጠርበት መንገድ ስሜን ለማጥፋት ዘመቻ ከፍተዋል።ሁኔታውን ከማህበሩና የኦዲተር ኮሚቴ አባላትና ከተሰበሰበው መስማትና መከታተል ይቻላል፤እነሱም ድምጻቸውን እንዲያሰሙ እጠይቃለሁ።ይህ ጽሁፍም የደረሳቸው ድህረ ገጾች የዚህን አይነት ኋላ ቀርና የበቀል ተግባር እንዲታረም  የኔን ማብራሪያ ለአንባቢ እንዲያቀርቡ በትህትና እጠይቃቸዋለሁ የአንዱን ብቻ እያስተናገዱ የሌላውን አለመስማትና እንዲሰማም አለማድረግ ወገናዊነትና የተዛባ አሠራር ይሆናል።በጋዜጠኝነት ስም አሉቧልታ የሚያናፍሰው ክንፉ አሰፋ የሚያደርገው ተደጋጋሚ  ጥፋት በሙያው የተሰለፉትን ሁሉ ስምና ሥራ የሚያጎድፍ ስለሆነ ከጋዜጠኝነት ሙያ እንዲወገድ ቢያደርጉት ለክብራቸው መልካም ነው።

በመጨረሻው ላይ ልገልጽ የምወደው በአሁኑ ጊዜ በጣም አንገብጋቢ ጉዳይ አለብን።ወያኔን ያህል ጠላትና አገር አድን ትግል በምናካሂድበት ወቅት በአንዳንድ ሰላዮች ተንኮል መጠመድ የለብንም።በያለንበት ከተማ የወያኔ ኤምባሲ ተንፈራጦ በነጻ መስክ የፈለገውን በሚያካሂድበት፣ወሬና መረጃ ለመሰብሰብ በሚችልበት ሁኔታ አንዳንድ ለጥቅም ያደሩ ልክስክሶች የሚያደርጉትን እርካሽ ምግባር ዋጋና ክብደት ልንሰጠው አይገባም።በተለይም በአደባባይ የምናደርገው ተቃውሞ ለወያኔ ባለሥልጣኖች የተሰወረ አይደለም፤ በየቤታቸው በእሳት ቴሌቪዥን ሳይቀር የሚተላለፈው ይደርሳቸዋል፣ያውቁታል።የፖለቲካ ፓርቲዎች ግን መጠንቀቅና ቤታቸውን ማጽዳት ያለባቸው እንደ ክንፉ አሰፋ የመሳሰሉትን ወራዳና ከመጣው ጋር መስሎ ለማደር የሚሯሯጠውን ፣በቂም በቀል ሰው ለማጥፋት የማይመለሰውን መምከር ወይም ማሶገድ ይኖርባቸዋል።ክንፉ አሰፋን የመሰሉ ሰዎች የሚሰበሰቡበት የፖለቲካ ድርጅት የብዙሃኑን  አመኔታና ድጋፍ እንዳያገኝ ይሆናል። ይኸው ልማደኛና መሰሎቹ የዛሬ ስድስት ዓመት የግንቦት ሰባት ንቅናቄ መሪ ዶር.ብርሃኑ ነጋ አምስተርዳም ለስብሰባ በመጣበት ጊዜ የወያኔ አባልና ደጋፊ ነው እያለ ሲያወግዘው የነበረ ሰው ነው።አሁን ግን ይህ አድርባይ እንደእስስት ቀለሙን ቀይሮ የብርሃኑ ነጋ ታማኝና አገልጋይ ለመሆን ይጥራል።ነገ ደግሞ ሌላ የሕዝብ ጆሮና ልብ የሚስብ ድርጅት ሲመጣ እንደበርሜል ከብለል ብሎ መፈክር ከመወርወር አይመለስም። እኔ አገሬ አዲስ ግን የምሠራውን ስለማምንበትና ስለማልፈራም ስሜን ለውጬ አልቀርብም፣አልጽፍምም።ጥቅምና ሹመት ፍለጋም ከአንዱ ድርጅት ወደሌላው በመሽከርከር ጊዜየን አላባክንም።ለገንዘብና ለስልጣን ጉጉትና ፍላጎት የለኝም።በኑሮ ያልተጎዳሁና በሥራዬ ውጤት እራሴን ችዬ የማድር ሰው ነኝ።  የሚያውቀኝ ሁሉ ሊመሰክር ይችላል።የማምንበትን በአደባባይና በግልጽ የምናገር ሰው ነኝ።አሁንም በኢትዮጵያ ልዑላዊነትና አንድነት፣በዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈን፣ለሰብአዊ መብት መከበር፣በወያኔ መወገድ አምናለሁ፤ እንደኔም የጸና እምነት ካላቸው ቁም ነገረኛ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን አብሮ በመሥራት ላይ ነኝ። የጀመርኩትንና የማምንበትን ትግል በአሉቧልታ ደንግጬ አላቆምም።

ትግላችን ከአሉቧልታና ከቂም በቀል የጸዳ ይሁን።ኋላ ቀር የተንኮል ሥራ የእውነተኛ የፖለቲካ ትግል ስልት አይደለም።

በተረፈ ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግ በማንኛውም ጊዜና ቦታ ቀርቤ ለማስረዳት ዝግጁና ፈቃደኛ ነኝ።

ወያኔና መሰሎቹ በጋራ ትግል ይወገዳሉ!!

እውነት ተደብቃ አትቀርም!!

ከሰላምታ ጋር

አገሬ አዲስ